# በዚህ ሳምንት ቅዳሜና ዕሁድ በኢሲምባ የውይይት መድረክ፦

Saturday & Sunday

December 1, 2007 >Room Opens @ 3:00 PM Eastern USA Time
December 2, 2007 >Room Opens @ 12:00 PM Eastern USA Time

## ለመሆኑ ጋጠ ወጡ ማነው?

በድርጅቶች የውስጥ ጉዳይስ ጣልቃ የገቡት ፤ ድርጅቶችን በማፍረስ የሚጠየቁትስ እነማናቸው? የደብተራው ድረ-ገጽ? ወይስ ሐማ ቱማ? ወይስ ኢሲምባ? እስኪ አስረዱን ፥

1. ሰሞኑን ዶ/ር ጌታቸው በጋሻው በየፓልቶኩ እየተዘዋወሩ ሁለተኛ ኢሕአፓ(ዴሞክራሲያዊ) ፤ ሁለተኛ ዴሞክራሲያ ያስፈለገበትን አንዱን ምክንያት ማለትም ኢሕአፓ በድርጅቶች ጣልቃ እንዲገባ ያደረጉት እነ ሐማ ቱማ በሕዝብ የተመረጡትን ወ/ሮ ብርቱካን ሚደቅሳን ስም እጥፍተዋል ለዚህም አንዳንድ ድረ-ገጾችንና የፓልቶክ መድረኮችን በስም እያነሱ ሲኮንኑ ተሰምተዋል።

   ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን ክስ በጥሞና እንመረምራለን። በየድረ-ገጾች ወጥተው ነበር የተባሉትን የሐማ ቱማን ጽሑፎች እናነባለን። ዶ/ር ጌታቸውና ግብረ-አበሮቻቸውን በይፋ ሰው አይቶአቸው ፀጋይ ሞቋቸው የክሳቸውን መረጃ መስመር በመሥመር ከኛ ጋር ሆነው አንብበው ፤ ወይም ሌሎች ፅሑፎችን በማቅረብ እንዲያስረዱን እነሆ በይፋ እንጋብዛቸዋለን።

2. ተጠያቂነት (Accountability) ምን ማለት ነው?
   ግልፅነት (Transparency) ምን ማለት ነው?
   ዴሞክራሲያዊ አሠራርስ ምን ማለት ነው?

3. የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዕውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያደርገው ትግል የት ላይ ደርሷል? ሁለት ቅንጅት ፤ ሁለት ኅብረት ፤ ሁለት ኢሕአፓ ፤ ሁለት ሲኖዶስ ፣ ሁለት ማርያም ወዘተ እየተሽቀዳደሙ ለመፍጠር ከሰማይ በታች ምክንያቶችንና ክሶችን የሚደረድሩና የሕብረተሰቡን ቅራኔ የሚያራግቡ መሪ ተብዬዎች እንደ አሸን በፈሉበት በዚህ ታሪካዊ ወቅትስ ከሀገር ወዳዶች ምን ይጠበቃል?